# በመንደር መሰባሰባችን…

ክፍል ሁለትና የመጨረሻ

ከሰለሞን ተስፋዬ 07-03-14

የከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክት በቻይናው ኮምፕላንት ኩባንያ ግንባታው እየተፋጠነ እንደሚገኝና የግንባታው አፈጻጸም ጥሩ ደረጃ ላይ በመሆኑ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል። የቻይናው የኮምፕላንት ኩባንያ አራት መቶ ቻይናውያንን በቦታው በማስፈር በውሉ መሠረት የፋብሪካው የመጀመሪያ ደረጃ ግንባታ አጠናቆ ለማስረከብ ቀንና ከሌት ሳይገድበው ሥራውን እያከናወነ ነው። የፋብሪካው የቦይለርና የተርባይን ተከላ ሥራዎች በመገባደድ ላይ ይገኛሉ። የፋብሪካው ግንባታ በቻይናው ኩባንያ ይከናወን እንጂ አገር በቀል ኮንትራክተሮችና ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ከቻይናዎቹ ጋር በፋብሪካው የግንባታ ሥራዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ።

የስኳር ፋብሪካው የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታው ሲጠናቀቅ በቀን ስድስት ሺህ ቶን አገዳ በመፍጨት በዓመት 163 ሺህ ቶን ስኳር የማምረት አቅም ይኖረዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ በሚካሄደው የማስፋፊያ ግንባታ ፋብሪካው በቀን የሚፈጨውን የሸንኮራ አገዳ ወደ አሥር ሺህ ቶን እንደሚያሳድገውና ዓመታዊ የስኳር ምርቱንም 250 ሺህ ቶን እንደሚያደርሰው ይጠበቃል ።

ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ የሚጠቀመው ይህ ፋብሪካ ከስኳሩ በተጓዳኝነት ኤታኖልና የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ለአገሪቱ ተጨማሪ የገቢ እሴትን የመፍጠር አቅም አለው። ፋብሪካው በዓመት 30 ሺህ ሜትር ኪዩብ ኤታኖል በማምረት አገሪቱ ለነዳጅ የምታወጣውን ወጪ በመቀነስ ረገድ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ፋብሪካው በሙሉ አቅሙ ማምረት ሲጀምር 39 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኋይል የማመንጨት አቅም ይኖረዋል፡፡

ፋብሪካው ለፍጆታው የሚፈልገውን ያህል የኤሌክትሪክ ኃይል በመጠቀምና የአካባቢውን ኅብረተሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ካደረገ በኋላ ቀሪውን 15 ሜጋ ዋት ኤሌክትሪክ ኃይል ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ቋት ያስተላልፋል። ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢው አርብቶ አደር ከስኳር ምርቱ የሚገኘውን ተረፈ ምርት ለእንስሳት ማድለቢያነት ለመጠቀም የሚያስችለውን ሁኔታ ለማመቻቸት የቅድመ ሁኔታ ሥራዎች እየተጠናቀቁ ይገኛሉ።

የአካባቢው ተወላጆች በፋብሪካው ግንባታ በተለያዩ ዘርፎች እንዲሳተፉ ፕሮጀክቱ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀሱ የአፋር ተወላጆች በሹፌርነት፣ በዶዘር ኦፕሬተርነትና በሜካኒክነት ሥልጠናዎች ተሰጥቷቸው በፕሮጀክቱ ተቀጥረው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ፕሮጀክቱ ከፍተኛ የሰው ኃይል ቅጥር እያደረገ ሲሆን በሰኔ ወር 2006 ዓ.ም ብቻ 500 ሠራተኞችን ለመቅጠር በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

ፋብሪካውን ከእርሻ ቦታዎቹና ከመኖሪያ ቤቶቹ ጋር የሚያገናኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ግንባታ ተካሂዶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ የፋብሪካውን ምርት ወደተፈለገበት ቦታ ለመውሰድ የሚያስችለውና ከዋና ዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኘውን የመንገድ መሠረተ ልማት ግንባታም እያደረገ ይገኛል። በዚህ መሠረትም ከፋብሪካው እስከ አዋሽ አርባ የሚያደርሰው 25 ነጥብ 2 ኪሎ ሜትር የአስፋልት መንገድ ግንባታ በመፋጠን ላይ ነው። ይህ ሥራ የሚከናወነው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አማካይነት ነው፡፡ ኮንትራቱን ሲጂኦሲ የተባለ የቻይና ኩባንያ ተረክቦ ግንባታውን እያከናወነ ነው፤ በታህሳስ ወር 2007 ዓ.ም ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል፡፡

የፕሮጀክቱ የመኖሪያና ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶች ግንባታም በዕቅዱ መሠረት እየተከናወነ ይገኛል። ግንባታውን እያከናወነ የሚገኘው ደግሞ የኦሮሚያ ኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ነው። እስካሁን ባለው መረጃ መሠረት 184 ቤቶች ግንባታ በማገባደድና አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ብሎኮች ግንባታ በመካሄድ ላይ ይገኛል። በከስም የስኳር ልማት ፕሮጀክት ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአካባቢው ከሥራና ተያያዥ በሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች ቋሚ ኑሯቸውን የጀመሩ ነዋሪዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ ጨመረ፤ አካባቢው ወደ ከተማነት እየተሸጋገረ መጣ።

ፋብሪካው ሥራ በሚጀምርበት ወቅትም የነዋሪው ብዛት በሦስት እጥፍ ያድጋል ተብሎ ይገመታል። የከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክት ተግባራዊ እንቅስቃሴውን በአፋር ክልል አሃዱ ብሎ ሲጀምር በቅድሚያ የአካባቢውን ኅብረተሰብ ማዕከል ያደረገ ልማትን በማምጣት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት በአንድ ደረጃ ከፍ የማድረግና አገሪቱ የያዘችውን የሕዳሴ ጉዞ ይበልጥ የማረጋገጥ ዓላማን ሰንቆ ነበር። መንግሥት የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ትላልቅ ልማቶች በመገንባትና አርብቶ አደሩን በልማቶቹ አካባቢ በማስፈር የተረጋጋ ሕይወትና ቋሚ ሰፈር እንዲኖረው ማድረግ ነው።

ቀደም ሲል ትኩረት ተነፍጎት የነበረው አርብቶ አደር ኑሮው የተመሠረተው የከብት ጭራን ተከትሎ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር ነበር። በዚህ መልክ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት መላክ የሚያስችል ሁኔታ አልነበረውም። የጤና፣ የንጹህ መጠጥ ውኃ፣ የትምህርትና ሌሎች አገልግሎቶች ተጠቃሚም አልነበረም። ይህንን ማዕከል ያደረገ ሥራ መከወን የተጀመረው ከኢህአዴግ መንግሥት መምጣት በኋላ ነው፡፡ ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የአርብቶ አደሩን አኗኗር ለመቀየር ከፍተኛ ሥራ ተሰርቷል።

በአገሪቱ ከሚገኙት የአርብቶ አደሮች አካባቢዎች አንዱ የአፋር ክልል ነው፡፡ በዚህ ክልል እየተገነባ ባለው የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ዙሪያ በመንደር የተሰባሰቡ አርብቶ አደሮች በአሁኑ ወቅት ወደ ከፊል አርሶ አደርነት እየተቀየሩ ይገኛሉ። ኅብረተሰቡ ከነበረው የተበታተነና ያልተረጋጋ የአኗኗር ዘይቤ ተላቆ የራሴ የሚለው መንደር መስርቶና መንደር ማሰባሰቡ ከተገነቡ የተለያዩ የአገልግሎት መስጫ ተቋማት አገልግሎት እያገኘ ሕይወቱን የሚመራበት ሁኔታ ተፈጥሮለታል። ለዚህ ደግሞ የአዋሽ አርባና የፈንታሌ ወረዳ ነዋሪዎች ከማንም በበለጠ ያውቁታል። ነዋሪዎቹ በአካባቢው እየተካሄደ ያለው ልማት ምን ያህል እንደጠቀማቸው በመረዳት ለሌላ ልማት መነሳሳታቸውን ይናገራሉ።

የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክትም መንግሥት በአገሪቱ የሚገኙ የአርብቶ አደር ማህበረሰቦችን ቀስ በቀስ ወደ ከፊል አርብቶ አደርነት ለመቀየር የሚያስችለውን ሥልት በመከተል ይበልጥ ውጤታማ እየሆነ መምጣቱን የሚያሳይ አንድ ትልቅ አብነት ነው።

ፕሮጀክቱ በአዋሽ ፈንታሌና ዱለቻ ወረዳ አካባቢዎች እውን መሆን ከጀመረበት አንስቶ በአፋር ብሔራዊ ክልል የዞን፣ የወረዳ፣ የቀበሌ አመራሮች፣ የአካባቢው ሽማግሌዎች፣ የጎሳ መሪዎችንና መላው የአካባቢው ኅብረተሰብን ያሳተፉ የተለያዩ የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ለኅብረተሰቡ የልማቱ ፋይዳና ዓላማ ግንዛቤ የማስያዙ ተግባር ውጤታማ ሆኖ አሁን በዚያ አካባቢ ያሉ ዜጎች ፀረ ሠላም ኃይሎች የሚያስተጋቡትን ማንኛውንም ዓይነት አፍራሽ ፕሮፖጋንዳ የሚሰማ ጆሮ እንደሌላቸው ይናገራሉ።

በፕሮጀክቱ አካባቢ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች ነዋሪዎች በልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በፈቃደኝነት ላይ መሠረት ያደረገ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም ተነድፎ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ የአካባቢው አርብቶ አደር ከከብት ጋር የተቆራኘውን የአኗኗር ዘይቤውን ሳይተው ከብቶችን እያረባ ጎን ለጎን የግብርና ሥራ እንዲያከናውን መግባት የሚያስችለው መሆኑን በመገንዘብ የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራሙን በሙሉ ልብ ተቀብሎት እየተሳተፈበት ይገኛል።

በአዋሽ ፈንታሌና ዱለቻ ወረዳዎች በሚገኙ የሣቡሬ፣ የደሆ፣ የቦሎይታና የቀበና ቀበሌ ነዋሪዎች በመንደር የማሰባሰብ ፕሮግራም አካል ናቸው። በእነዚህ ቀበሌዎች የሰፈሩ ሦስት ሺህ የሚሆኑ አርብቶ አደር አባወራዎችና እማወራዎች የማህበራዊ አገልግሎት ሙሉ ተጠቃሚ ሆነዋል። መጠቀማቸውን በተግባር እያዩ ሲመጡና የልማቱ ትሩፋት ተቋዳሽ መሆናቸውን ሲያስተውሉ ተሳትፏቸውን እያጠናከሩ መጥተዋል። ነዋሪዎቹ የከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክት ስኬትን በጉጉት የሚጠብቁት ሆኗል።

በሣቡሬ ቀበሌ የሚገኙ ሦስት መቶ አርብቶ አደር አባወራዎችና እማወራዎች በተመቻቸላቸው የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም በመጠቀም በአሁኑ ወቅት ሽንኩርት፣ ቲማቲምና በቆሎ በማምረት በአንድ ጊዜ ሽያጭ እስከ መቶ ሺህ ብር ድረስ ማግኘት በመቻላቸው በመንደር መሰባሰባቸው እንደጠቀማቸው ይናገራሉ፡፡ አቶ በልአ ሰያሌ በሣቡሬ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። ፕሮጀክቱ ሲጀመር መደናገር እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡ “ያኔ የተለያዩ አፍራሽ ሃሳቦች በተለያዩ ወገኖች ይቀርቡ ስለነበር ጠቀሜታው ብዙም አልታየንም ነበር። ውሎ አድሮ መንግሥት በፈጠራቸው የውይይት መድረኮች ባገኘነው ግንዛቤ በሂደትም ከልማቱ ተጠቃሚ

እየሆን መምጣታችንን ስናይ ግን እውነትም መንግሥታችን የኛን ሕይወት ለመቀየር ቆርጦ መነሳቱን ለመረዳት ችለናል” ይላሉ። የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ለነዋሪው እያስገኘ ያለው ፋርጀ ብዙ ጠቀሜታ የነዋሪውን አኗኗር እየለወጠ ነው። እያንዳንዱ አባወራና እማወራ አርብቶ አደር  አንድ ሄክታር መስኖ ገብ መሬት  በማግኘቱ ከከብት ሽያጭ በተጨማሪ  በግብርና ሥራ ገቢ ማግኘት ችሏል ይላሉ ነዋሪው።

በደሆ ቀበሌ ደግሞ 755 አባወራዎችና እማወራዎች ይገኛሉ። እነዚህ አርብቶ አደሮች በመንደር ማሰባሰቡ ፕሮግራሙ በመታቀፋቸው  የመሠረታዊ  ማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ተጠቃሚ መሆን ችለዋል። የጤና ኬላዎች፣  የመስኖ ውኃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የወፍጮ አገልግሎት፣ የመንገድ፣ የትምህርት ቤትና የእምነት ተቋማት ግንባታዎች ተካሂደው በእነዚህ ተቋማት እየተገለገሉ ይገኛሉ። ይህ ዓይነት ሁኔታ ቀደም ሲል ያልነበረ እንደሆነም ነዋሪዎቹ ይገልጻሉ።

አንዲት እናት በወሊድ ምክንያት ለሚያጋጥማት ችግር የሕክምና እርዳታ የምታገኝበት ምንም ዓይነት የጤና ተቋም በአካባቢው አለመኖሩን የሚገልጹት ነዋሪዎቹ ወደ ከተማ ለመውሰድ ቢፈለግ እንኳን የመንገድና የትራንስፖርት ችግር በመኖሩ የተነሳ ሕክምና ያለበት ቦታ ሳትደርስ ለሕልፈተ ህይወት ትዳረግ ነበር ይላሉ። ይህ ሁኔታ አሁን ከታሪክ የዘለለ አልሆነም፤ በአካባቢያችን የጤና ጣቢያ በመገንባቱና ባለሙያዎች በመመደባቸው ሕክምናውን በቅርበት ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ መፈጠሩ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ አድርጓል ብለዋል ።

የደሆ ቀበሌ ነዋሪ ወጣት አሊ አሙድ አሲ በበኩሉ ባለፉት ሥርዓታት የአፋር ኅብረተሰብ ትኩረት ከተነፈጉ የአገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንዱ ነበር። አሁን…አሁን የተሻለና ዘመናዊ ሕይወትን እየተቋደሰ መጥቷል። በተለይ ከከሰምና ሌሎች በክልሉ እየተገነቡ ካሉ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች እያገኘ ያለውን ጥቅም ከፍተኛ በመሆኑ ከማንም የበለጠ ራሱ ይመሰክራል ብሏል። በቦሎይታና በቀበና ቀበሌዎችም ከ1800 በላይ አባወራና እማወራ አርብቶ አደሮች የማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ተገንብቶላቸውና የመስኖ ገብ መሬት ተሰጥቷቸው የተሻሻለ ኑሮን እየገፉ ይገኛሉ።

የከሰም ስኳር ልማት የፕሮጀክት ውጤት የሆነው የመንደር ማሰባሰብ ፕሮግራም ከጨለማ ወደ ብርሃን እንድንጓዝ አድርጎናል ይላሉ የአካባቢው ነዋሪዎች። እናቶች በጤና ባለሙያዎች እንዲወልዱ የጤና ኬላ አገልግሎት መጀመሩንና በአካባቢው የወፍጮ አገልግሎት በመኖሩ የሴቶች የሥራ ጫና በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱንም በአንደበታቸው ይመሰክራሉ። የአካባቢው አርብቶ አደር በማህበር እንዲደራጅ በማድረግ በአገዳ አብቃይነት ስራ ለማሰማራት በመንግስት እየተደረገ ያለው ጥረት ተስፋ ሰጪ ነው ይላሉ። በማህበር የተደራጁ አርበቶ አደሮችም ቀደም ሲል ስራው ከጀመሩ የወንጂ የስኳር ፋብሪካ አካባቢ ነዋሪዎችን ተሞክሮ እንዲያገኙ መደረጉን ፕሮጀክቱ ገልጿል ።

ፕሮጀክቱ የአርብቶ አደሩን የልማቱ ተጠቃሚነት ይበልጥ ለማሳደግ አርብቶ አደሩ በተሰጠው መስኖ ገብ መሬት ሸንኮራ አገዳ በማልማት ምርቱን ለፋብሪካው እንዲያቀርብና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን ለማሳደግ እየተጋ ይገኛል። የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ኅብረሰሰቡን የሥራ ዕድል ተጠቃሚ ለማድረግ ከሚችሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶች አንዱ ነው፤ እስካሁን ፕሮጀክቱ በእርሻና በመስኖ ሥራዎች፣ በቤቶች ግንባታ፣ በፋብሪካ ግንባታና ተያያዥ ዘርፎች ከ15 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ለአካባቢው ማኅበረሰብ አለኝታ መሆን ችሏል።

ፕሮጀክቱ የአካባቢ ጥበቃን ማዕከል ያደረገ ሥራን ለማከናወን ከሸንኮራ አገዳ በተጓዳኝ ማንጎና ብርቱኳን እያለማ ይገኛል። ባለፈው ዓመት ብቻ ከማንጎ ሽያጭ ስምንት ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ችሏል። የተገኘውን ገቢ ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር በማቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ለማከናወን እየተጠቀመበት ነው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት አገራዊ ፋይዳ በተናጠል የሚታይ አይደለም። ከሌሎች መሰል ፕሮጀክቶች ጋር ተደምሮ የሚታይ እንጂ። የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ከሌሎች በመላ አገሪቱ እየተገነቡ ካሉ የስኳርም ሆነ ሌሎች ትላልቅ የልማት አውታሮች ጋር ተደምሮ በአገሪቱ የኢንዱስትሪ መሠረት ለመጣል የሚኖረው ፋይዳ የጎላ ነው። በተለይ የአገራችንን የስኳር ፍጆታ በማረጋገጥ የሚኖረው አስተዋጽኦ በቀላል የሚታይ አይደለም። ከዚህም ባሻገር ምርቱን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ገቢዋን በማሳደግ በኩል ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

የስኳር ፋብሪካው ለጅቡቲ ወደብ ካለው ቅርበት አንጻርም ከሌሎቹ ፋብሪካዎች በተለየ መልኩ ጠቀሜታውን ያጎላዋል። የፋብሪካው የስኳር ምርት በቀላሉ ወደ ውጪ አገራት ማስተላለፍ ይቻላል። ይህም የመጓጓዣ ወጪን በከፍተኛው ደረጃ ስለሚቀንስ ኢኮኖሚያዊ አዋጭነቱን የላቀ እንደሚሆን ባለሙያዎች ይገልጻሉ። በአጠቃላይ የከሰም ስኳር ልማት ፕሮጀክት ለአካባቢው ኅብረተሰብ የሚኖረው ጠቀሜታ ዘርፈ ብዙ ነው። ፋብሪካው በሚፈጥረው የሥራ እድል በመሳተፍ፤ በመስኖ ውኃ ተጠቅሞ ሌሎች ሰብሎችን በማምረት፣ የሸንኮራ አገዳ እያመረቱ ለፋብሪካው ማቅረብና ከፋብሪካው የሚገኘውን ተረፈ ምርት ለተለያዩ ጥቅሞች በማዋል ረገድ የአካባቢውን ነዋሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ።

ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ተበታትኖ የነበረ ሕዝብ የራሴ በሚለው አካባቢ ሰፍሮ ጠንካራ ማህበራዊ ቁርኝት ፈጥሮና በችግርና በደስታ ጊዜ ተደጋግፎ ለመኖር ያስችለዋል። በአካባቢው የጤና አገልግሎት ማግኘቱ፣ የትምህርት እድል መከፈቱ፣ የንጹህ መጠጥ ውኃ ማግኘቱ፣ የመንገድና ሌሎች መሠረተ ልማቶች ተጠቃሚ መሆኑ ከዚህ ፕሮጀክት ጋር ተያይዘው የመጡ ናቸው። በቀጣይ አካባቢው ወደ ከተማነት እየተለወጠና የሕዝቡ የአኗኗር ዘይቤም ሙሉ በሙሉ እየተቀየረ መምጣቱ የማይቀር ሂደት ይሆናል። ይህ ደግሞ መንግሥት የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመቀየር የያዘው ስትራቴጂ አካል መሆኑ እሙን ነው። ነዋሪዎቹም ከዚህ የተለየ ሃሳብ የላቸውም። ቀደም ሲል የነበራቸው የተበታተነ ምቹ ያልሆነ አኗኗር በመንደር ከሰፈሩ በኋላ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል።

ቀደም ሲል ለከብቶቻችን ቀለብና ውኃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ያልተረጋጋ ኑሮ እንኖር ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን ለከሰም የስኳር ልማት ፋብሪካ እየተገደበ ካለው ውኃ በፈለግነው መጠን ማግኘት በመቻላችን በአንድ ቦታ ተረጋግተን ከብቶቻችንን ማርባት ችለናል። ከዚሁ ጎን ለጎንም በግብርና ምርት ላይ እየተሳተፍንና እየተጠቀምን እንገኛለን። በመንደር መሰባሰባችን በርካቶች ይፈጥሩት ከነበረው ውዥንብር በተቃራኒው ተጠቃሚ አድርጎናል። በልማቱ በሰፊው ተጠቃሚ መሆናችንን በተግባር አይተነዋል። በመሆኑም በአካባቢያችን በመካሄድ ላይ ያሉ ልማቶችን በግንባር ቀደምትነት ለማገዝ እየሰራን እንገኛለን ይላሉ የአዋሽ ፈንታሌ ነዋሪዎች። እርግጥ ነው፤ ከብትን ተከትሎ ከመኖር ተሰባስቦ

መኖር በርካታ ኢኮኖሚያዊና  ማህበራዊ ጠቀሜታ ይሰጣል። በተለይ አርብቶ አደሩ የነበረው ሕይወት የተበታተነና ያልተረጋጋ፤ የእኔ የሚለው ቋሚ መንደር ያልነበረው ስለነበር  በመንደር መሰባሰቡ የበለጠ ተጠቃሚ እንደሚያደርገው እሙን ነው። ለዚህ ደግሞ በአርብቶ አደሩ አካባቢ እየተካሄዱ ያሉ እንደ ከሰም የስኳር ልማት ፕሮጀክት የመሳሰሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶች የአካባቢውን ነዋሪዎች ሕይወት በመለወጥ ረገድ ፋይዳቸው የጎላ ነው።